# ጊዜ ያለፈበት የ COVID-19 ምርመራዎች ተደጋጋሚ ጥያቄዎች

**ጊዜ ያለፈበት የ COVID-19 ምርመራዎችን አሁንም አይጣሏቸው። የ COVID-19 ምርመራዎ አሁንም በሳጥኑ ላይ ከተዘረዘረው የአገልግሎት ማብቂያ ቀን በኋላም ለመጠቀም ጥሩ መሆኑን የሚያውቁባቸው መንገዶች እነሆ።**

## ጊዜ ያለፈበትን የ COVID-19 ምርመራ መጠቀም እችላለሁ?

አዎ። የ Washington State Department of Health (DOH፣ የዋሺንግተን ግዛት የጤና መምሪያ) ምርመራው የጥራት ቁጥጥር እስካለፈ ድረስ ያለፉትን ምርመራዎች ለመጠቀም ይፋዊ ማጽደቂያ አውጥቷል (በእንግሊዘኛ)።

በተጨማሪም፣ አንዳንድ የ COVID-19 ምርመራዎች የመጠቀሚያ ጊዜ ማራዘሚያዎችን ከ U.S. Food and Drug Administration (FDA፣ የአሜሪካ የምግብ እና መድኃኒት አስተዳደር) ያገኛሉ፣ ይህም ለምርመራዎቹ በሳጥኑ ላይ ከምታዩት የተለየ አዲስ የማብቂያ ቀናትን ይሰጣል። የትኛዎቹ ምርመራዎች የዘመነ የአገልግሎት ማብቂያ ቀን እንዳላቸው ለማየት FDA የምርመራዎች ዝርዝር ከተራዘመ የመጠቀሚያ ጊዜ (በእንግሊዘኛ እና ስፓኒሽ) መፈለግ ይችላሉ። ምንም እንኳን አንድ ምርመራ አሁን የዘመነ ጊዜ ያለፈበት የአገልግሎት ማብቂያ ቀን ቢኖረውም፣ በ DOH መሰረት፣ የጥራት ቁጥጥር ካለፈ አሁንም ምርመራውን መጠቀም ይችላሉ።

ቁልፍ ነጥብ፦ አብሮ ያለውን የጥራት ቁጥጥር ፍተሻ እስካለፈ ድረስ፣ ጊዜ ያለፈበትን ምርመራ መጠቀም ይችላሉ።

## ጊዜ ያለፈበት የ COVID-19 ምርመራ ትክክለኛ ውጤቶችን እንደሚሰጠኝ እንዴት አውቃለሁ?

የእርስዎ የ COVID-19 ምርመራ ምርመራው በአስተማማኝ ሁኔታ መሥራቱን ለማረጋገጥ በሚወስዷቸው እርምጃዎች ላይ መመሪያዎችን ይዞ ይመጣል፣ ይህም "የጥራት ቁጥጥር" ይባላል። ብዙውን ጊዜ የጥራት ቁጥጥር ሂደቱን በምርመራ መመሪያው ሉህ ላይ ባለው የምርመራ ውጤት ክፍል ውስጥ ማግኘት ይችላሉ። ለብዙ በቤት ውስጥ ለሚደረጉ ምርመራዎች የጥራት ቁጥጥር ሂደት በመመርመሪያ መያዣ ላይ ከሚታተመው "C" ቀጥሎ ያለው መስመር ናሙናው በሚወርድበት ጊዜ እንደሚታይ ማረጋገጥ ነው። የጥራት ቁጥጥር ሂደቱ ካልተሳካ፣ መመርመሪያውን መጣል አለብዎት።

## የመመርመሪያ የተራዘመ የአገልግሎት ጊዜ እንዴት ያገኛል?

የ COVID-19 መመርመሪያዎች አምራቾች አንድ መመርመሪያ ለምን ያህል ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል የሚመለከቱ ጥናቶችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። FDA ይህን ውሂብ የሚከታተለው የተራዘሙ የአገልግሎት ቀናትን ለማጽደቅ ነው። እነዚህ መመርመሪያዎች ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ ተጨማሪ መረጃ ስለሚመጣ፣ ለ COVID-19 መመርመሪያዎች የአገልግሎት ጊዜ ማራዘሚያዎች የተለመዱ ናቸው።

ይህ መረጃ በሳጥኑ ላይ ባለው የአገልግሎት ማቢቂያ ቀን መሰረት፣ ጊዜ ያለፈባቸው የሚመስሉ መመርመሪያዎችን ሲጠቀሙ ያረጋግጥልዎታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። አሁን የ COVID-19 መመርመሪያዎ ለመጠቀም ጥሩ መሆኑን ለማየት ምን ማድረግ እንዳለብዎት ያውቃሉ፦ በቀላሉ የጥራት ቁጥጥር የምርመራ መመሪያዎችን ይከተሉ። መመርመሪያው የጥራት ቁጥጥር ካለፈ አሁንም ደህንነቱ የተጠበቀ እና ለመጠቀም ጥሩ ነው።

የማህበረሰቦቻችንን ደህንነት እና ጤና ለመጠበቅ ለሚያደርጉት ሁሉ እናመሰግናለን!

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ በ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም ኢሜይል በ civil.rights@doh.wa.gov ይላኩ።

DOH 421-037 February 2023 Amharic